# የቀለም አብዮት-ሂዩማን ራይትስ ዎችና የልብ ወዳጆቹ

**ታከለ አለሙ**

Tigrai Online December 15, 2013

ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ እንደሚለው የአገሬ ሰው “ራሱን የሰብአዊ መብት አስጠባቂ” ሲል ሰይሞ እ.ኤ.አ. በ1978 “ሄልንስኪዎች” በሚል ቢቋቋምም የድርጅቱን ውስጠ ምስጢር ገላልጠው ጥናት ያካሄዱበት ተመራማሪዎች ግን ተቋሙ የሚያከናውነው ተግባርና ለራሱ የሰጠው ስያሜ ፍፁል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ ይሉት አይነት እንደሆነ በይፋ አጋልጠውታል።ራሱ ድርጅቱ “የሰብዓዊ መብት መመሪያዎችን የሚጥስ ” ተቋም መሆኑን ከተቋቋመበት ጊዜ እስካሁን ድረስ ባሉት ጊዜያት በአለም ላይ ባሉ የተለያዩ አገራት ያከናወናቸውን ተግባራት አብጥረጥረው በተጨባጭ በማሳየት።

የቀድሞው “ሄልንስኪዎች” የአሁኑ ሂዩማን ራይትስ ዎች ዓለም በምዕራቡና በምስራቁ ጎራ በተከፋፈለችበት ጊዜ በያኔዋ ሶቭየት ህብረት የሚመራውን የምስራቁን ጎራ ለማዳከም ራሳቸውን “የኢምፔሪያሊዝም ወኪሎች” እያሉ በሚጠሩ የሊበራሊዝም አቀንቃኝ ሃይሎች “ፎርድ ፋውንዴሽን” ከተሰኘ ኩባንያ በተገኘ 400 ሺህ ዶላር የመነሻ ገንዘብ እኤአ በ1978 እንደተቋቋመ ይነገርለታል።

ፎርድ ፋውንዴሽን እኤአ በ1970ዎቹና በ1980ዎቹ አሜሪካ በአለም አቀፍ ደረጃ የሰብአዊ መብት ለማስጠበቅ በሚል ሂዩማን ራይትስ ዎችን ጨምሮ “Watch Groups” በሚል ስያሜ የሰብአዊ መብት እናስጠብቃለን በሚል እንዲመሰረቱ ላደረገቻቸው ድርጅቶች ከተሰበሰበው የገንዘብ ድጋፍ የአንበሳውን ድርሻ እንደሰጠ እኤአ በ1993 Kathryn Sikkink የተባሉ ምሁር ባሳተሙት የምርምር ጽሁፍ ላይ ይፋ አድርገዋል።

Kathryn Sikkink በዚሁ ፅሁፋቸው ታድያ የፎርድ ፋውንዴሽን መስራቾችና ከፍተኛ አመራሮች የሚታወቁት በፀረ ዴሞክራሲያዊነታቸው ሆኖ ሳለ ሂዩማን ራይትስ ዎችን ጨምሮ የተለያዩ “ዎች ግሩፕስ” በሚል ስያሜ የሚጠሩ የሰብአዊ መብት እንዲያስጠብቁ በሚል ለተመሰረቱ ተቋማት የሚውል ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ ድጋፍ እንዴት ሊሰጥ ቻለ ? የሚለውን ጥያቄ በማንሳት በእርግጥስ እነዚህ ተቋማት ቀደም ሲል የተገለፀውን የሰብአዊ መብት ጉዳይ በተግባር የማስጠበቅ ጉዳይ ላይ የመንቀሳቀሳቸው ሁኔታ ምን ያህል እውነትነት አለው በሚል ከፍተኛ ጥርጣሬ በአለም ዓቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ እንዲፈጠር አደረጉ።

በተለይም እነ ሂዩማን ራይትስ ዎች የተፈጠሩበት እኤአ የ1970ዎች ወቅት የኒዮ ሊበራል አይዲዎሊጂ የሚከተሉ አንዳንድ ምእራባውያን አገራት ልእልናቸውን ለማስጠበቅ የሞት የሽረት ትግል ላይ የነበሩበት ወቅት ከመሆኑ አንፃር እነ ሂዩማን

ራይትስ ዎች በእርግጥም በሰብአዊ መብት ሽፋን ለፖለቲካ አይዲዎሎጂ ማስጠበቂያ ተቋቋመው ይሆናል የሚለውን ጥርጣሬ ይበልጥ እንዲጎላ አደረገው።

በእነ ፎርድ ፋውንዴሽን ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ የተቋቋመው ሂዩማን ራይትስ ዎች ከተመሰረተ በሁዋላም የስራ ማስኬጂያውም ሆነ አጠቃላይ አስተዳደራዊ ወጪው በቀለም አብዮት አባትነቱ በሚታወቀው ጆሮጅ ሶሮስና መሰል ባለሃብቶች በተገኘ በርካታ ቢሊዮን ዶላር መሸፈኑ ደግሞ ድርጅቱ የሰብአዊ መብት ተቋም ስላለመሆኑ እንደ ተጨማሪ ማስረጃ አገለገለ።

እንደሚታወቀው ጆሮጅ ሶሮስ የተሰኘው ቢሊዮነር በአለም ላይ የታወቀ የቀለም አብዮት አባት ሲሆን “ሁሉንም ነገር ለገበያውና ለባለሀብቱ መተው አለበት፤መንግስት ህግና ስርዓትን ከማስከበር ባለፈ ኢኮኖሚው ውስጥ እጁን ማስገባት የለበትም” በሚል የገበያ አክራሪነ መርህ የኒዮ ሊበራል አይዲዎሎጂን ለማስጠበቅ በአለም ላይ ያሉ አገራትን በሙሉ በማስገደድም ቢሆን የዚህ አይዲዎሎጂ ተከታይ እንዲሆኑ ለማድረግ በቢሊዮኖች  የሚቆጠር ግዙፍ ሃብቱን በማፍሰስ የሚንቀሳቀስ አምባገነን ነው ።

በመሆኑም Kathryn Sikkink እና መሰል በእነ ሂዩማን ራይትስ ዎች ላይ ምርምርና ጥናታቸውን ማካሄድ የቀጠሉ ምሁራን በየጊዜው ያወጧቸው የነበሩ የምርምር ፅሁፎች እነዚህ ተቋማት የሰብአዊ መብት ጥበቃን ለስውር ፖለቲካዊ አጀንዳቸው በሽፋንነት እንደተጠቀሙበት በማጋለጥ ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።

ታድያ ሂዩማን ራይትስ ዎች ለፖለቲካል አይዲዎሎጂ ማስጠበቂያ እንጂ ለሰብአዊ መብት ጥበቃ ያለመቋቋሙን ውስጠ ሚስጥር ገላልጠው በጥናታቸው ከፈተሹት ምሁራን መካከል አንዱ የሆኑት ሚስተር ማይክል ባርከር እኤአ በ2007 “ Hijacking Human Rights” በሚል ባሳተሙት ጥናታዊ ፅሁፍ  ላይ የሚከተለውን አስፍረው ነበር ፡፡

ሂዩማን ራይትስ ዎች “በአለም ላይ ለሰው ልጆች ዴሞክራሲና ለሰብዓዊ መብቶች ቆሜያለሁ በሚል ይሰብክ እንጂ ዴሞክራሲን ከማያውቁ የኢምፔሪያሊዝም ሃይሎች ጋር በወኪልነት የተሰለፈ እንደ መሆኑና በጀቱን የሚመድቡለትም በፀረ ዴሞክራሲነት የሚታወቁ ጥቂት ቡድኖችና ቱጃሮች ከመሆናቸው አንፃር የሚያከውናቸውም ተግባራት እነዚህ ሃይሎች በተለያዩ አገራት የውስጥ ጉዳይ ላይ ጣልቃ እንዲገባ በሚሰጡት ትእዛዝ ላይ በማተኮር ነው ፤ በዚህም ሳቢያ በተለይም በአሁኑ ወቅት ድርጅቱ የኢምፔሪያሊዝም ወኪሎች የሆኑ ጥቂት ቡድኖችና ግለሰቦች የኪስ ማደለቢያና ፀረ-ዴሞክራሲያዊ የሆኑ ተቋማት ጉዳይ ማስፈፃሚያ ተቋም እየሆነ ቢመጣም ተቋሙ ይህንን ያወቀው ግን እጅግ ዘግይቶ ነበር ” ሲሉ ገልፀውታል።

ሌሎች በድርጅቱ ላይ ጥናት ያካሄዱ ምሁራንም ሂዩማን ራይትስ ዎች ራሱ እንደሚለው  ሰብዓዊ መብትን ለማስጠበቅ የቆመ ሳይሆን የኒዮ ሊበራሊዝም አይዲዎሎጂን ለማስጠበቅ ሲል የራሳቸውን የፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ መስመር ቀይሰው በሚንቀሳቀሱ አገራት ላይ የማያቋርጥ የሃሰት ዘመቻ እየከፈተ ዛሬ ላይ የደረሰ ተቋም እንደሆነ ነው የሚያወሱት።

ሂዩማን ራይትስ ዎች ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የራሳቸውን መስመር ቀይሰው የሚንቀሳቀሱ አገራት በዜጎቻቸው ላይ ከፍተኛ የሆነ የሰብአዊና የዴሞክራሲያዊ መብት ጥሰት እንደፈፀሙ በማስመሰል ያለ ማቋረጥ በሚያካሂዳቸው የሃሰት ውንጀላዎች ሃያላን አገራት እርዳታና ብድር መስጠትን ጨምሮ ሌሎች ዲፕሎማሲያዊና መሰል ግኑኝነቶች እስከማቋረጥ የሚደርሱ ጫናዎችዎችን እንዲያሳድሩባቸው ያለማቋርጥ ይወተውታል።

እነዚህ አገራት በጫና ተንበርክከው የኒዮሊበራልን መስመርን እስኪከተሉ ድረስም ሁሉንም ዓይነት ማስገደጃዎችን በመጠቀም ከመስመራቸው እንዲያፈገፍጉና እንዲንበረከኩ ያለመታከት ሌት ተቀን ይሰራል፤ የተቻለውን ያህል ይታትራል ።

በዚህ የድርጅቱ እንቅስቃሴ ሰለባ ከሆነ የአለም  አገራት መካከል ባለፉት ሃያና ሰላሳ አመታት ከኒዩ-ሊበራሊዝም አይዲዎሎጂ ውጭ ራሳቸው በቀየሱት ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ መስመር ተጉዘው ፈጣንና ተከታታይ እድገት ያስመዘገቡት ቻይናና የኤስያ አናብስት (The Asian Tigers) ይጠቀሳሉ።

እንደሚታወቀው ከቀዝቃዛው ጦርነት ፍፃሜ በኋላ የኤስያ አናብስቶቹና የቻይና መንግስታት የራሳቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ ነው ያሉትን ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ መስመር ነድፈው ተግባራዊ በማድረግ ለስኬቱ ህዝባቸውን በስፋት አንቀሳቅሰዋል።

በዚህም ጥረታቸው ላለፉት ሰላሳ አመታት ፈጣንና ተከታታይ የሚባል የኢኮኖሚ እድገት አስመዝግበዋል። በዚህም መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለመሰለፍ ባቀዱት ጊዜ ውስጥ ለመቀላቀል በቅተዋል። ይህም በአሁኑ ወቅት በተለይም ቻይና ኢኮኖሚዋ በከፍተኛነቱ ከሚታወቀው የአሜሪካ ኢኮኖሚ ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆን አስችሏታል።

ይሁን እንጂ ቻይና ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ እድገት ባስመዘገበችባቸው ያለፉት ሰላሳ አመታት ጉዞ እንዲሁ አልጋ በአልጋ አልነበረም፤ በእነዚህ አመታት ሂዩማን ራይትስ ዎችና መሰል ፅንፈኛ የአክራሪው የኒዮ ሊበራል ሃይል ጋር በመተባበር የሃሰት ሪፖርትና መግለጫ በዴሞክራሲና በሰብዓዊ መብት ሽፋን የዘመቻ ናዳ ሲያውርድባት እንደነበር የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ከጥቂት አመታት በፊት በቻይና ከተካሄደው ኦሎምፒክ በፊት በቲቤት የግዛት ጥያቄ ሽፋን የተቀሰቀሰውን “የክሪምሰን አብዩት” በማቀጣጠል ሂዩማን ራይትስ

ዎችና መሰሎቹ ጉልህ አሉታዊ አስተዋፅኦ ማድረጋቸውን በመስኩ የተካሄደው ጥናት ያረጋግጣል።

ሆኖም ግን የቻይና መንግስት ይህን መሰል ጫናዎችንና ዘመቻዎችን በመቋቋም ከቀየሰው የልማት መስመር ሳያፈንግጥ የአገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት ግስጋሴ በአለም ግዙፍ ከሚባሉት ኢኮኖሚዎች ተርታ እንዲሰለፍ አስችሎታል።

የኤስያ አናብስት በመባል የሚታወቁት አገራትም የተቋሙና መሰል አክራሪ ፅንፈኛ ተቋማት የሃሰት ሪፖርትና መግለጫ ሰለባ በመሆን ረገድ ከቻይና የተለየ ተሞክሮ የሌላቸው ቢሆንም ይህ የሃሰት ዘመቻ ግን ከመስመራቸው ፈቅ እንዲሉ አላደረጋቸውም።

ለዚህ ነው ሚስተር ጁሊ ሜርትስ የተባሉ ፀሐፊ ሂዩማን ራይትስ ዎች የራሳቸውን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ መስመር ቀይሰው በመጓዝ ውጤታማ የሆኑ አገራት ላይ በሰብዓዊ መብት ሽፋን የሚከፍታቸውን ዘመቻዎች በመጥቀስ መግለጫዎቹና ሪፖርቶቹ ከድርጅቱ ተግባርና ባህሪያት ጋር አብረው የማይሄዱ፣ መንታ አቋም ያላቸው፣ከግልፅነት ይልቅ የሰውን ልጅ ተፈጥሮ ፍርሃት የሚያላብሱና ለአጭር ጊዜ መሳሪያነት የሚውሉ ብቻ ናቸው ሲሉ በአፅንኦት በጥናታዊ ፅሁፋቸው ላይ ያሰፈሩት ።

ሂዩማን ራይትስ ዎች ምንም እንኳን ተሳክቶለት ውጤታማ መሆን ባይችልም ቀደም ሲል በተጠቀሰው መልኩ ለረዥም ዘመናት የሀሰት ዘመቻ ከከፈተባቸው የኤስያ አናብስት( Asian Tigers) እና ቻይና በተጨማሪ የቀለም አብዮት እስከ መቀስቀስ የሚዘልቀው የዚሁ ዘመቻው ሰለባ በመሆን ደግሞ ዩክሬንና ጆሪጂያንን ይጠቀሳሉ ።

እ.ኤ.አ. በ2007 ኸርማን ፣ ፒተርሰን እና ዛሙሊ የተባሉ ፀሐፍት ሂዩማን ራይትስ ዎችን አስመልክቶ ባሳተሙት ጥናት ድርጅቱ በሰብዓዊ መብት ሽፋን በዩጎዝላቪያ ባካሄደው ጣልቃ ገብነት አገሪቱን ለመበታተን ያበቃትን አሉታዊ አስተዋፅኦ ማበርከቱን አስረግጠው ገልፀዋል ።

ምሁራኑ በዚሁ ጥናታቸው ሂዩማን ራይትስ ዎች በዩጎዝላቢያ “ለሰብዓዊ መብት መጠበቅ ቆሜያለሁ” የሚለው ይህው ተቋም በአገሪቱ የተቀሰቀሰውን የእርስ በእርስ ግጭት እንደ ምቹ አጋጣሚ በመጠቀም እ.ኤ.አ. ከ1992 ጀምሮ ሰብዓዊ መብቶች የሚዳከሙበትን ሁኔታዎች በማመቻቸት እንዲሁም በወቅቱ የሰሜን ቃል ኪዳን አባል ሀገራት ጦር (ኔቶ) በአገሪቱ ላይ የፈፀመውንና “ከፍተኛ ዓለም አቀፍ ወንጀል” የሚባለውን ተግባር እንዲያከናውን መደላድል ፈጥሯል።

በዚህም ሳቢያ ተቋሙ ከሚሰብክለት የሰብዓዊ መብት መርህ በተቃረነ የዩጎዝላብውያንን መብት በመጣስ ረገድ ግንባር ቀደም ተሳታፊ እንደነበረም ግልፅ አድርገው በፅሁፋቸው አሳይተዋል።

በተመሳሳይ በዩክሬንም “ብርቱኳናማ አብዮት” በማቀጣጠል ለበርካታ ሰዎች ህልፈተ-ህይወት ምክንያት ሆኗል። ተቋሙ በተለይም ከቅርብ አመታት ወዲህ ደግሞ ዋና ተግባሩ የሆነውን የቀለም አብዮትን በአፍሪካ አንዳንድ አገራትም ከማካሄድ እንዳልተጠቀጠበ ጥናቶች ይጠቅሳሉ

በተለይም በዚምባባዌና በኬንያ ተቋሙ የሚፈልጋቸውን ለእርሱ የሚሽከረከር አሻንጉሊት መንግስት ለመመስረት በተንቀሳቀሰበት ወቅት የበርካታ ሰዎች ደም በእነዚህ አገራት በከንቱ እንዲፈስ አድርጓል።

ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ የኒዮሊበራል አይዲዎሊጂን ከማስጠበቅ ውጭ የሰው ልጆች የሰብአዊ መብትና መጠበቅና መከበር ቅንጣት ታህል አሳስቦትና አስጨንቆት የማያውቀው ሂዩማን ራይትስ ዎች በኢትዮጵያም መንግስትም ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እውን ካደረገበት ካለፉት አመታት እስካሁን ባሉት ጊዜያት የሰብአዊ መብት ማስከበር በሚለው ሽፋኑ በመንቀሳቀስ በአገራችን ላይ ዘመቻ ያላካሄደበትን ጊዜ ለማስታወስ ይቸግራል።

በጀት የሚመድቡለትን የኒዮ ሊበራል አጀንዳ አሃይሎች ለማሳካት ሲል በተለይ ምርጫ በተቃረበ ቁጥር መድረክን የመሳሰሉ ተቃዋሚዎች ላይ በመንጠላጠል ባለፉት ጊዜያት በአገራችን ለማቀጣጠል ተሞክሮ የጨነገፈውን የቀለም አብዩት ለመቀስቀስ ተስፋ ሳይቆርጥ ይሰራል።

ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአትን በአገሪቱ ተግባራዊ ያደረገው የኢትዮጵያ መንግስት እጅ በመጠምዘዝ አይዲዎሎጂያቸውን ለመጫን ለሚፈልጉ ሃይሎች ፊት የማይሰጥ በመሆኑም በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት በሃይል በመጣል እንደፈለገ ከውጭ ሆኖ በሪሞት ኮንትሮል ሊያንቀሳቅሰው የሚችል ሃይል አፈላልጎ በማግኘቱ ምርጫ በመጣ ቁጥር ተስፋ ሳይቆርጥ ይህንን ሃይል አብዮት ቀስቅሶ ስልጣን ላይ ሊያወጣው ያልማል ፤ ይቃዣል ፤ ይወራጫል።

ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ተቋሙ በፀረ ዴሞክራሲ ሃይሎች የተመሰረተ ከመሆኑ አንፃር በዴሞክራሲያዊ መንገድ በህዝቦች ተሳትፎ የሚደረግ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ተቃርኖ በፀረ ዴሞክራሲያዊ መንገድ እርሱ የሚፈልገውን ሃይል በቀለም አብዮት ታግዞ አፍራሽ ሃይሎችን “ዙፋን አንጋሽ” በመሆን በህዝቦች ጫንቃ ላይ ለመጫን ይማስናል፤ ለዚህ አላማው ደግሞ አንዳንድ የምዕራብ ሚዲያዎችን በመሳሪያነት ይጠቀማል።

በኢትዮጵያ በሚቀጥለው አመት የሚካሄደው የ2007 አገር አቀፍ ምርጫ ታሳቢ በማድረግ ከያዝነው አመት መጀመሪያ እስካሁን ድረስ ባሉት አራት ወራት ጊዜ ውስጥ የታራሚዎች ሰብአዊ መብት አያያዝ ተጥሷል ከሚለው ጀምሮ የጋዜጠኞች መብትንና በቅርቡ ከሳውዲ ተመላሽ ዜጎቻችን ጋር የተያያዘውን ጨምሮ አራት ያህል የሃሰት መግለጫዎችንና ሪፖርቶችን አውጥቷል።

ባለፈው ጥቅምት ወር የታራሚዎች መብትንና የፀረ ሽብር ህጉን አስመልክቶ ያወጣውን  ሪፖርት መድረክም ከሳምንታት በሁዋላ ለጋዜጠኞች በሰጠው መግለጫ እንዳለ ኮፒ አድርጎ ማውጣቱ እንደተለመደው በተለይም ምርጫ ሲቃረብ በእነዚህ ሃይሎች መካከል የሚፈጠረውን ቅንጅትና ለቀለም አብዮት ቅስቀሳ የሚደረገውን ዝግጅት የሚያመላክት እነዚህን ሁኔታዎች መንግስት ልብ ሊላቸው እንደሚገባ ለመጠቆም እወዳለሁ።

በተለይም በቅርቡ በአፍሪካ፣ ካሪቢያን፣ የፓስፊክና የአውሮፓ ህብረት ፓርላማ የጋራ ጉባኤ 26ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ በአዲስ አበባ ለመካፈል ተገኝተው የነበሩት ወይዘሮ አና ጎሜዝም ከእነ ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ በአገር ውስጥ ካሉ ፅንፈኛ የተቃዋሚ ሃይሎችና ከአገር ውጭ ከሚገኙ አሸባሪ ቡድኖች ጋር በጋራ ለ2007 አም ምርጫ ቀለም አብዮት ቅድመ ዝግጅት የሚሆናቸውን እንደ “የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል፤ ተቃዋሚዎች ታፍነዋል፤  የሲቪል ማህበረሰቡ በምርጫ እንቅስቃሴ ውስጥ አስተዋፅኦ ሊያደርግ ይገባል“          የሚሉና የመሳሰሉት መግለጫዎቻቸው ሲታዩ በእርግጥም የእነዚህ ሃይሎች ቅንጅት በጉልህ እየታየ ነውና መንግስትም ምርጫው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የሚያካሂድበትን ሁኔታ ከወዲሁ ሊያስብበት ይገባል እላለሁ።